THE ALEXANDRIA POLICE DEPARTMENT

# በበዓል ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ ወንጀሎችን የመከላከል እቅድ

የእርስዎ የሆነው የአሌክሳንድሪያ ፖሊስ መምሪያ ፣የትራፊክ ደህንነት ጥሰቶችን፣ ስርቆትን፣ ዘረፋዎችን እና በበዓል ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ ወቅታዊ ወንጀሎችን ጨምሮ ለመከላከል እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ የሚቆይ ከተማ አቀፍ የበዓል ወቅት ደህንነትን የማረጋገጥ እንቅስቃሴ እየጀመረ ነው።

ዓላማችን በበዓላት ወቅት በአሌክሳንድሪያ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ, የሚሰሩ እና ሊጎበኙ የሚመጡ ሰዎችን ደህንነት መጠበቅ እና ከተማችን እንግዳ ተቀባይ መሆኗን ማረጋገጥ ነው።

ወንጀልን ለመከላከል እና በበዓላት ወቅት የትራፊክ ደህንነት ህጎችን ለማስከበር ተጨማሪ ጥበቃ በሚያስፈልጉባቸው ቦታዎች ላይ ትኩረት እናደርጋለን። ይህም የሚከናወነው ከዚህ በታች በተገለጸው መሠረት ነው:-

### በአካል መገኘት

በገበያ ማዕከላት እና የንግድ ኮሪደሮች፣ በመኖሪያ እና በመተላለፊያ ኮሪደሮች ውስጥ በእግር፣ በብስክሌት፣ እና የሚንቀሳቀሱ ፓትሮል መኮንኖችን ያያሉ።

### ስልታዊ ሕግ ማስከበር

በተደጋጋሚ ወንጀል የሚፈጽሙ ወንጀለኞችን ለመያዝ እና በመንገዶቻችን እና በመላ ከተማው ላይ ሕግን ለማስፈጸም ያለፈ እና የአሁን የወንጀል መረጃን እየተጠቀምን ነው።

### በማህበረሰባዊ ተሳትፎ

ፖሊሶች፣ ከነዋሪዎች ከንግዶች እና ከአጎራባች ማህበራት ጋር እየተገናኙ ግንዛቤን እና ተሳትፎን ለማሳደግ አብረው ይሰራሉ።

### በቴክኖሎጂ እገዛ

ቴክኖሎጂን መጠቀምፖሊሶች(መኮንኖች) ስልታዊ እና ቀልጣፋ ምላሽ እንዲሰጡ ለመርዳት፣ የጥበቃ ስራዎችን ለማጠናከር እናየማህበረሰባችንን ደህንነት ለመጠበቅ ወንጀልን ለመከላከል እንደ ሃይል ማባዣነት ይረዳል።

## እርስዎም እንዲሳተፉ እንጠይቃለን።

### ወደ ቤትዎ የሚላክለዎትን እሽግ ወይም ጥቅል እቃዎችን መድረሳቸውን በደንብ ይከታተሉ

ሊቆለፉ የሚችሉ የእቃ ማስቀመጫወችን ይጠቀሙ ።የሚላክለወትን እሽግ እቃዎች መድረሳቸውን ይከታተሉ። እርስዎ የማይኖሩ ከሆነ የሚያምኑት ጎረቤትዎ እቃውን ተቀብሎ እንዲያስቀምጥልዎ ያመቻቹ።

### ንቁ ይሁኑ

ወደ ተሽከርካሪዎ ሲሄዱ ሀሳብን ወይም ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ያስወግዱ። ብርሃን በደንብ ያላቸው አካባቢዎችን ይጠቀሙ ። በእግር በሚራመዱበት ወይም መኪና በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የስልክ የጽሑፍ መልእክት ከመላክ ይቆጠቡ።ሁልጊዜም የመኪና ቁልፎትን ዝግጁ ያድርጉ ።

### መኪናዎትን ይጠብቁ

ሁልጊዜም መኪናዎን መቆለፋን ያረጋግጡ: ውድ የሆኑ ንብረቶች እና ዕቃዎችን ከተሽከርካሪዎት ውስጥ ያስወግዱ። የመኪናዎንሞተር ካላጠፉ ያለ ጠባቂ ትተውት አይሂዱ።

### ያልተለመደ እና አጠራጣሪ እንቅስቃሴዎችን ሲመለከቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያድርጉ

አጠራጣሪ ወይም ትክክል የማይመስል እንቅስቃሴ ካዩ, እባኮዎን ለፖሊስ ይጠቁሙ— ምናልባትም የእርስዎ ጥቆማ ወንጀልን ሊከላከል ይችላልና። ድንገተኛ ያልሆኑ ጉዳዮችን ለመጠቆም በዚህ ቁጥር ይደውሉ# 703-746-4444

## በአደጋ ጊዜ 9-1-1 ይደውሉ።
## ድንገተኛ ያላልሆኑ ጉዳዮችን ሪፖርት ለማድረግ በዚህ ቁጥር ይደውሉ: 703-746-4444